የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28[th] Year No. 37
ADDIS ABABA 31[st] May, 2022

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፭፻፲፭/፪ሺ፲፬
የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ ደንብ........ገጽ ፲፬ሺ፪፻፵፮

## Content

Regulation No. 515/2022
Definition of Organization, Power and Duties of Education and Training Authority Regulation ……..............................Page 14246

## ደንብ ቁጥር ፭፻፲፭/፪ሺ፲፬

## የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፷ (፪) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ ደንብ ቁጥር ፭፻፲፭/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## REGULATION No. 515/2022

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE DEFINITION OF ORGANIZATION, POWER AND DUTIES OF EDUCATION AND TRAINING AUTHORITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 60 (2) of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.1263/2021.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Definition of Organization, Power and Duties of Education and Training Authority Regulation No. 515/2022."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 64.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ባለሥልጣን" ማለት የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ነው፤

፪/ "የትምህርትና ሥልጠና ጥራት" ማለት በሀገሪቱ የሚሰጠውን አጠቃላይ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እና በከፍተኛ ትምህርት የሚሰጠው ትምህርት በስታንዳርድ መሠረት ማስጠበቅ ነው፤

፫/ "አጠቃላይ ትምህርት" ማለት በሀገሪቱ በቅድመ መጀመሪያ ደረጃ፣ በመጀመሪያ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ መደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ የትምህርት መርሀ ግብር የሚሰጥ ትምህርት ነው፤

፬/ "ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና" ማለት በሀገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት በማንኛውም የሙያ ዘርፍ ደረጃቸው ከከፍተኛ ትምህርት በታች በሆኑ መደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ መልኩ የሚሰጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እንዲሁም የሙያ ብቃት ምዘና ሥርዓት ሲሆን መደበኛ ባልሆነ መልኩ የተገኘ የሙያ ብቃት የማረጋገጥ ሥርዓትን ይጨምራል፤

፭/ "ደረጃ ምደባ" ማለት ለአጠቃላይ ትምህርት ጥራት አጠባበቅ በሚዘጋጁ መሥፈርቶች መሠረት ትምህርት ቤቶችን በመመዘን የሚሰጥ ደረጃ ነው፤

## 2. Definition

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1/ **"Authority"** means Education and Training Authority;

2/ **"Education and Training Quality"** means the country makes asure quality standard of the general education, technical and vocational trainings of the country as well as higher education to be rendered in this regard;

3/ **"General Education"** means pre-primary, primary, secondary as well as formal and informal education to be rendered in the country;

4/ **"Technical and Vocational Training"** means technical and vocational education and training to be delivered as per the country's educational and training policy at every level of professions in form of formal or non-formal means of training as well as process of assessing occupational competence and, includes assessment of occupational competence that has been acquired through non-formal means;

5/ **"Ranking"** means rank given to the schools based on the requirements of general education quality assurance standards;

፮/ "ፈቃድ" ማለት በትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ለሚሰማሩ ተቋማት የሚሰጥ የትምህርትና ሥልጠና የሥራ ምዝገባ ነው፤

፯/ "እውቅና" ማለት

ሀ) በከፍተኛ ትምህርት መስክ ፈቃድ አግኝቶ ሲሠራ የቆየ ተቋም ወይም የትምህርት መስክ በባለሥልጣኑ የወጣውን የጥራት ስታንዳርድ ስለማሟላቱ ተገምግሞ የሚሰጥ የጥራት ማረጋገጫ፤ ወይም

ለ) በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋሞች የሚሰጡ የሥልጠና መርሃ ግብሮች የእውቅና አሰጣጥ መመሪያ አንጻር ተመዝነውና ተገቢነታቸው ታይቶ በባለሥልጣኑ የወጣውን የጥራት ስታንዳርድ ስለማሟላቱ ተገምግሞ የሚሰጥ የጥራት ማረጋገጫ ሲሆን፣ የሙያ ብቃት ምዘና ማዕከላት ምዘና ለማከናወን ያላቸው ብቃት ተመዝኖ ማረጋገጫ የሚያገኙበት አሠራርንም ይጨምራል፤

ሐ) ተቋማዊ ኢንስፔክሽን በማካሄድ በሚገኘው ውጤት መሠረት ለአጠቃላይ ትምህርት ተቋማት የሚሰጥ የጥራት ማረጋገጫ ነው።

፰/ "ጥራት ኦዲት" ማለት የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ወይም ፕሮግራም ውጤታማ የጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት ዘርግቶ እየተገበረ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚደረግ ግምገማ ነው፤

፱/ "የትምህርት ማስረጃ ማረጋገጥ" ማለት ከሀገር ውስጥ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም የተገኘን የትምህርት ማስረጃ ሕጋዊና ትክክለኛ ስለመሆኑ መመስከር ነው፤

6/ **"License"** means a registration given to the institutions which engage in education and training sector;

7/ **"Accreditation"** means

a) Accreditation to be given to existing educational institutions or other institutes acquired recognition in accordance with requirements of the Authority after the necessary evaluation; or

b) Accreditation to be given to technical and vocational trainings institutions programs shall be evaluated in accordance with the set forth Directives to carryout monitoring activities with regard to their compatibility. Accreditation shall include quality of the educational institutes; it also includes accreditation to Competency Assessment Centers.

c) Accreditation to be given to the overall educational institutions based on institutional inspection result in terms of quality standard.

8/ **"Quality Audit"** means the process of systematic examination of a quality system of an educational and training institution or a program;

9/ **"Authentication of Educational Credentials"** means to verify authenticity and legality of educational credential offered by any licensed or accredited local education and training institutions;

፲/ **"አቻ ግመታ"** ማለት

ሀ) ከሀገር ውስጥ ወይም ከውጪ ሀገር ለተገኘ የትምህርት ማስረጃ የሚሰጥ ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ ነው፤

ለ) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የውጤት ተኮር ስትራቴጅ ስለሚከተል ለአጠናቃቂ ሰልጣኝም ሆነ ለአሰልጣኝ ባለሙያ ለደረጃው ብቁ መሆኑ የሚረጋገጠው ለየደረጃው በሚሰጥ የሙያ ብቃት ምዘና ይሆናል፤

፲፩/ **"ደረጃ ስያሜ"** ማለት ለከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚሰጥ የዩኒቨርሲቲ፣ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፣ የኮሌጅ እና የኢንስቲቲዩትነት ስያሜ ወይም ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም የሚሰጥ የፖሊቴክኒክ፣ የኮሌጅ ወይም የኢንስቲትዩትነት እንዲሁም በኢንስቲቲዩት ውስጥ አጫጭር ሥልጠናዎችን የሚሰጡ ተቋማትን የሚጨምር ስያሜ ነው፤

፲፪/ **"ተቋም"** ማለት የመንግስት ወይም የግል የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ነው፤

፲፫/ **"የመንግስት ተቋም"** ማለት እንደአግባብነቱ በጀት በፌደራል ወይም በክልል መንግስት የሚመደብለት የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ነው፤

፲፬/ **"የግል ተቋም"** ማለት በአንድ ግለሰብ ወይም ከአንድ በላይ ቁጥር ባላቸው ሰዎች ባለቤትነት ወይም በውጭ ሀገር ተመስርቶ በኢትዮጵያ ውስጥ ፈቃድ አግኝቶ የሚንቀሳቀስ የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ነው፤

10/ **"Equivalence"** means

a) meritorious verification of educational credential acquired in the country or from abroad to its most proximate local counterpart;

b) technical and vocational education and trainings oriented shall be focused on completion of the study, thus the required qualification certificate shall be given to the trainee who completed the study and to the trainer in order to make sure that who has the required qualification;

11/ **"Status"** means naming higher education institution either as university, university college, college and institute; or other technical and vocational and educational trainings as polytechnic, college or institute. It also includes institutes that provides short term Trainings;

12/ **"Institution"** means governmental or private educational and training institution;

13/ **"Public Institution"** means education and training institution to which budget is assigned by the federal or regional state as the case may be;

14/ **"Private Institution"** means an education and training institution which is run and owned by one or more persons or established abroad and operating in Ethiopia with a license;

፲፭/ "ለትርፍ ያልተቋቋመ ተቋም" ማለት ዓላማው ለትርፍ ያልሆነ በግለሰብ ወይም ማህበራት ወይም በህብረት ሥራ ማህበራት ወይም በንግድ ማህበራት ወይም አግባብነት ባለው ሕግ የተመሠረተ ወይም በውጭ ሀገር ተመስርቶ በኢትዮጵያ ውስጥ ፈቃድ አግኝቶ የሚንቀሳቀስ የትምህርትና ሥልጠና ተቋም ነው፤

፲፮/ "ቦርድ" ማለት በዚህ ደንብ አንቀፅ ፰ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የተቋቋመ የባለሥልጣኑ የስራ አመራር ቦርድ ነው፤

፲፯/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ጨምሮ እንዲሁም በሕግ አግባብ የሚቋቋሙትን አዲስ ክልሎችን ያካተተ ነው፤

፲፰/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፱ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፡፡

## ፫. ዋና መስሪያ ቤት

የባለሥልጣኑ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ በሀገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

15/ **"Non-profitable Institution"** means an institute which is established to operate individually or in association or in cooperative association or other forms of associations to provide services without aiming generation of profit, as it is established and incorporated in Ethiopia with license issued in the country concerning educational and training activities;

16/ **"Board"** means a board of management of the authority established as per Article 8 Sub-Article (1) of this Regulation;

17/ **"Region"** means any region situated in Ethiopia as stipulated on constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Article 47 including Addis Ababa and Dire Dawa City Governments and other new regions;

18/ **"Ministry" or "Minister"** means the Ministry or Minister of Education respectively;

19/ **"Person"** means natural person or legal entity;

20/ Any expressions in masculine shall include feminine expression as well.

## 3. Head office

The Authority's Head Office is located in the city of Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

**፬. <u>ተቋማዊ ነጻነት</u>**

ባለሥልጣኑ የትምህርትና ሥልጠናን ጥራት ለማስጠበቅ በሚያደርገው እንቅስቃሴ እና በሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ከማንኛውም ሰው ወይም አካል ወይም አደረጃጀት ጣልቃ ገብነት ነፃ ነው፡፡

**፭. <u>የባለሥልጣኑ ዓላማ</u>**

የትምህርትና ሥልጠና ጥራት የሚመራበትን ሕግ በማሻሻልና የጥራት፣ የግምገማ፣ ክትትልና ቁጥጥር በማከናወን የሀገሪቱ የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ማረጋገጥ ነው፡፡

**፮. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የትምህርትና ሥልጠና ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያግዝ የስታንዳርድ ማዕቀፍ፤ ጋይድላይን እና መገምገሚያ መስፈርት ያወጣል በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤

፪/ በትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ፡-

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ በሚንቀሳቀስ ማንኛውም የመንግስትና የግል እንዲሁም ከውጭ ለሚመጣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋምና የትምህርት ፕሮግራም፤

**4. <u>Institutional Independence</u>**

The authority is independent from any sort of interferences and intervention to be made by any individual or organ with regard to its decision in assuring quality of education and trainings.

**5. <u>Objective of the Authority</u>**

By improving the legal framework which governs education and training, it will be assuring quality of education and training by performing activities related to education quality monitoring, evaluation and control in the country.

**6. <u>Powers and Duties of the Authority</u>**

The Authority has the following power and duties:

1/ Approve standards, procedural system, guidelines and checklists, and follow up their implementation to ensure quality of education and training;

2/ In regard to education and training sector:

a) issue license, renew license, conduct supervision and cancel their license program accreditation to any Public Higher Education Institution and program accreditation and institutional license to Private Higher Education Institutions operating in Ethiopia, for higher education institutions comes from abroad wishing to involve in the education and training sector;

ለ) በፌደራል ደረጃ ለሚቋቋም እና ከውጭ ሀገር ለሚመጣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋምና የሥልጠና መስክ፣ እና

ሐ) ለማሕበረሰብና ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶች አጠቃላይ ትምህርት፣

ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ቁጥጥር ያደርጋል፣ የተሰጠውን ፈቃድ ወይም እድሳት ይሰርዛል፤

፫/ ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና በማቋቋም ኃይማኖት ነክ ያልሆነ ትምህርትና ሥልጠና ለመስጠት የሚፈልግ የኃይማኖት ተቋም በባለሥልጣኑ የፈቃድ እውቅና አሰጣጥ መመሪያ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ቁጥጥር ያደርጋል፣ እንደአስፈላጊነቱ የተሰጠውን ፈቃድ ወይም እድሳት ይሰርዛል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ለተጠቀሱት ተቋማት ተቋማዊና የፕሮግራም ጥራት ኦዲት ያከናውናል፣ እንዲሁም በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሐ) ለተጠቀሱት ተቋማት ኢንስፔክሽን ሥራን ያከናውናል፤ በተገኘው ውጤት መሠረት ዕውቅና ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ተቋም ላይ ድንገተኛ ጉብኝት ያደርጋል፤

b) issue license, renew license, conduct supervision and cancel license to Technical and vocational educations and training institutions to be established at the federal level or from abroad;

c) issue license, renew license, conduct supervision and cancel their license to Community and international schools to be established at the federal level or from abroad;

3/ Any religious institution that intends to deliver non-religious trainings shall grant license or accreditation, renew the license, conduct supervision and cancel their license accordingly based on the Directives applicable to the license or accreditation;

4/ Carryout institutional and program quality audit to institutions indicated under Paragraph (a) and (b) of Sub-Article 2 of this Article and shall provide accreditation; shall carryout inspection work regarding activities indicated under Paragraph (c) of Sub-Article 2 of this Article; provide recognition, renewal, cancellation; execute evaluation pursuant to findings of the audit at any time;

፭/ የክልል የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ተቆጣጣሪ አካላት በባለሥልጣኑ የሚወጡ ስታንዳርዶች ተግባራዊ መደረጋቸውን በሱፐርቪዥን ይከታተላል፤

፮/ ከሀገር ውስጥ ተቋም የተገኘ የትምህርት ማስረጃ ሕጋዊነትና ትክክለኛነት ያረጋግጣል፤ ከውጭ ሀገር ተቋማት ለተገኙ የትምህርትና ሥልጠና ማስረጃዎች እና ከሀገር ውስጥ ለተገኙ የአቻ ግመታ ለሚያስፈልጋቸው የትምህርትና ሥልጠና ማስረጃዎች የአቻ ግመታ ይሰጣል፤

፯/ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ፈቃድ ለሰጣቸው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የደረጃ ስያሜ ይሰጣል፤ በአጠቃላይ ትምህርት ሥራ ለተሰማሩ ተቋማት የደረጃ ምደባ ያደርጋል፤

፰/ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት እና ከኢትዮጵያ ውጭ ካሉ ሌሎች አካላት ጋር የትምህርትና ሥልጠና ጥራትን ለማረጋገጥ በትብብር ይሠራል፤ በሕግ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች መካከል በውክልና ለሌሎች አካላት ማስተላለፍ ይችላል፤ ብቃታቸውን ይገመግማል፤ ፈቃድ ይሰጣል፤ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፈቃዳቸውን ይሰርዛል፤

5/ Carryout supervisions on implementation of the Authority's standards by the regional education and training quality supervising bodies;

6/ Authenticate legality and genuineness of academic credentials issued in the country; carryout equivalent evaluation to foreign academic credentials and to local credentials that might require equivalence;

7/ Designate status of higher education institutions as well as to technical and vocational education institutions and designate ranking of general education schools licensed by the Authority;

8/ Work in collaboration with governmental and non-governmental stakeholders in Ethiopia as well as other organs out of Ethiopia to assure quality standard of provision of education and trainings; In addition, the Authority is entitled to transfer its powers to other legal organs as per provisions of the law, it is also entitled to evaluate, issue license, monitor their efficiency and cancel their licenses when it deemed necessary;

፱/ የትምህርትና ሥልጠና ጥራትን ለማረጋገጥና ለማጎልበት የሚያግዙ ጥናትና ምርምሮችን ያከናውናል፤

፲/ የትምህርትና ሥልጠና ምሩቃን የሙያ ብቃት ምዘና የሚካሄድበት የአሠራር ሥርዓት ማዕቀፍ ያዘጋጃል፤ ይህንን ለሚሰሩ አካላት ፈቃድ ይሰጣል፤እንዲሁም በትምህርትና ሥልጠና ጥራት ሊያማክሩ ለሚችሉ አካላት ዕውቅና ይሰጣል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤ ሥራቸውንም በበላይነት ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፈቃዳቸውን ይሰርዛል፤

፲፩/ ከሀገር ውጭ ያሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትንና የአቻ ተቋማትን ጥራት ለመፈተሽ የውጭ ገምጋሚ አካል ሆኖ ሊሠራ ይችላል፤እንዲሁም ባለሥልጣኑ የአሠራር ሂደቱን በቀጠናው ወይም በአህጉሩ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ባሉ አቻ የጥራት ማረጋገጫ አካላት ያስገመግማል፤ ሥራውንም ለማሻሻል ይጠቀምበታል፤

፲፪/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በሚወሰነው መሠረት ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያ ያስከፍላል፤

፲፫/ ሥልጣን ባለው አካል የሚወጡ የተማሪዎች ቅበላን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ተቋማት ተግባራዊ ማድረጋቸውን ይቆጣጠራል፤

፲፬/ ተቋማት ስለሚተገብሩት ሥርዓተ ትምህርት፣ የትምህርት ፕሮግራሞቻቸው ዝርዝር፣ የአካዳሚክ ሰራተኞቹ፣ ደረጃና የቅጥር ሁኔታቸውን መረጃ ይወስዳል፣ ለተማሪዎች እና ለህብረተሰቡ ተገቢውን መረጃ መድረሱን ያረጋግጣል፣ ይከታተላል፤

9/ Conducting of various researches and surveys to ensure quality standard education and trainings in the country;

10/ Establish system of evaluating professional competencies for education and training graduates; issue license for and regulating institutions in charge of undertaking evaluation; and shall give recognition to organs that may involve in education and training advisory activities; evaluate and monitor their efficiency and cancel their licenses when deemed necessary;

11/ May function as external quality auditor to audit the quality of higher education institutions and equivalent quality assurance institutions abroad; as well as it may carryout evaluation works at regional or continental or international level by equivalent organizations;

12/ Implementation of service charges according to Council of Ministers Regulation;

13/ Supervise institutions on the implementation of Directives pertaining to students' admission as enacted by relevant authorities;

14/ Collect institutions' information related to their implemented curriculum, list of programs, level of academic employees, employment status of the academic employees and keep this information open for the students and the community;

፲፭/ ተቋማት ባለስልጣኑ የሚጠይቃቸውን መረጃዎች ያለምንም ክፍያ በሚፈልግበት ዓይነትና በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረባቸውን ይቆጣጠራል፤

፲፮/ ተቋማት የመክሰር ውሳኔ እንዲሰጥበት ጥያቄ ከቀረበበት ወይም የመከፈል ወይም የመዋሃድ ወይም የመስፋፋት ወይም ትምህርት የሚሰጥበት ቦታን የመቀየር ወይም የባለቤትነት መብት የማስተላለፍ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ይህንኑ ወዲያውኑ ለባለስልጣኑ የማሳወቅ ሂደት መተግበራቸውን ይቆጣጠራል፤

፲፯/ ተቋማት ፈቃድ ወይም እውቅና አግኝተው ሲሠሩና በተጨማሪም ሥልጠና ለመስጠት የሚፈልጉ ከሆነ ሥልጠና የሚሰጥበትን ፕሮግራምና ጊዜ ይቆጣጠራል፤

፲፰/ በዚህ ደንብ ድንጋጌዎችና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት ማንኛውም ተቋም የውስጥ ጥራት ማረጋገጥ ሥርዓት መዘርጋቱንና መተግበሩን ይቆጣጠራል፤

፲፱/ ማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም በጥራት ማረጋገጥ ረገድ በአጠቃላይ ትምህርት አሰጣጥ፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና አሰጣጥ፣ በከፍተኛ ትምህርት አሰጣጥ ምርምር እና በማኅበረሰብ አገልግሎት ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ተጠያቂነት እና ኃላፊነትን በተመለከተ በወጣው መመሪያ መሠረት መስራቱን ያረጋግጣል፤

15/ Supervise institutions to offer free of charge any information to the Authority in the form they are requested and, in a file, format required within the time limit the Authority requested them to be submitted;

16/ Monitor the implementation of the requirement to notify the Authority any judgment of bankruptcy, decision for separation or merger or expansion or change of campus or ownership title transfer cases as soon as they exist;

17/ Oversee where an institution which has already been licensed or accredited wish to commence additional trainings, it shall monitor the program and its training schedule;

18/ It shall discharge its duties and responsibilities based on relevant provisions of this Regulation and other laws which apply to the case to supervise institutions on their established system of internal quality assurance;

19/ Ensure that educational and training institutions deliver appropriate educational, technical and vocational trainings as well as execution of surveys on the delivery of higher educaton, researches and community service activities in accordance with provisions of responsibilities and accountabilities, pursuant to the set forth provisions of the Directive;

፳/ የማንኛውም የትምህርትና ሥልጠና ተቋም በፈቃድ አሰጣጥ፣ በእውቅና፣ በደረጃ ስያሜ ወይም የደረጃ ምደባ እና ሌሎች አቤቱታና ቅሬታዎችን በመቀበል ያያል፤

፳፩/ የተሠሩ ሥራዎችና የተገኙ ውጤቶች እንዲሁም የተወሰዱ ሕጋዊ እርምጃዎችን በተገቢ መረጃዎችን በልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎች ለማህበረሰቡ ተደራሽ ያደርጋል፤

፳፪/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤እንዲሁም ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

፮. <u>የባለሥልጣኑ አደረጃጀት</u>

ባለሥልጣኑ፡-

፩/ የሥራ አመራር ቦርድ (ከዚህ በኋላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ)፤

፪/ ዋና ዳይሬክተር፤

፫/ እንዳስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና

፬/ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል፡፡

፯. <u>የቦርዱ አባላት</u>

፩/ ቦርዱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሰብሳቢና አባላት ይኖሩታል፤

፪/ የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን ፬ ዓመት ይሆናል፤

፫/ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባል እና ጸሐፊ ይሆናል፡፡



20/ Receive and see grievance and complain related to educational and training institutions on their license, accreditation, and status, ranking and related issues;

21/ Keep record of the services provided and results of evaluations undertaken; address required legal measures to the public with topical information using a range of pertinent media;

22/ Own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name; undertake other related activities which are essential for the achievement of its objectives.

7. **<u>Organization of the Authority</u>**

The Authority shall have :

1/ A Board of management (hereinafter referred to as the "Board");

2/ Director General;

3/ Deputy Directors as may be necessary; and

4/ Other necessary employees.

8. **<u>Members of the Board</u>**

1/ The Chair person and members of the Board shall be appointed by the Prime Minister;

2/ The tenure of the members of the Board shall be 4 years;

3/ The Director General of the Authority shall be member and secretary of the Board.

**፱. የቦርዱ ሥልጣንና ተግባራት**

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ የባለሥልጣኑን ዕቅዶችና ሪፖርቶች ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤

፪/ ባለሥልጣኑ በሚያመነጨው የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ማረጋገጥ ማዕቀፍ ላይ ይመክራል፤

፫/ ስታንዳርድና የአሠራር ሥርአቶችን ያፀድቃል፤ ተግባራዊነታቸው ይከታተላል፤

፬/ ለባለሥልጣኑ ሥራዎች የሚያስፈልጉ በቂና ብቁ የሰው ኃይል፣ የገንዘብ፣ የቴክኖሎጂና የቁሳቁስ ሀብቶች እንዲሟሉለት ጥረት ያደርጋል፡፡

**፲. የቦርዱ ስብሰባ**

፩/ የሥራ አመራር ቦርዱ ስብሰባ በወር አንድ ጊዜ ይካሄዳል፤ እንዳስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

፪/ ከሥራ አመራር ቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ የሥራ አመራር ቦርድ ውሳኔ በስብሰባው በተገኙት አባሎች አብላጫ ድምፅ ይወሰናል፤ ቦርዱ በድምፅ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

፬/ የሥራ አመራር ቦርዱ የራሱን የአሰራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**9. Power and Duties of the Board**

The Board shall have the following power and duties:

1/ Follows up; Monitor on the implementations of plans and reports of the Authority;

2/ Discuss on the framework of educational and training quality assurance;

3/ Approve standards and guidelines; and follow up their implementations;

4/ Cause fulfillment of sufficient and qualified human resource, finance, technology and material resources the Authority requires to deliver its business.

**10. Meeting of the Board**

1/ The Board shall meet once in every month; provided, however, it may meet urgently at any time as may be required.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members are present at a meeting of the Board.

3/ Decisions of the Board shall be passed by majority votes of the members present at a meeting; provided, however, that the Chairperson shall have a casting vote in case of a tie.

4/ The Board may adopt its own directive of procedure.

## ፲፩. የዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባር

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ በመሆን የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ ደንቡ የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የባለሥልጣኑን ሠራተኞችን በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል ያስተዳድራል፤

ሐ) የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚደረግ ግንኙነት ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ) የባለሥልጣኑን የሥራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ያቀርባል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለሥራ ቅልጥፍና ሲባል ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 11. Power and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Authority, and shall direct and administer the activities of the Authority.

2/ Without limiting the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the power and duties specified under Article 6 of this Regulation;

b) employee and administer employees of the Authority based on the Federal Civil Service Law;

c) Prepare operational plan and budget of the Authority and submit it to concerned government bodies and implement same up on approval;

d) Effect payments in line with the budget and operational plan approved for the Authority;

e) Represent the Authority in all its dealings with third parties;

f) Prepare performance and financial reports, and present it to concerned government organ;

3/ The Director General may delegate part of his powers to other officers and staff of the Authority to the extent it is desirable for expeditious accomplishment of the activities of the Authority.

## ፲፪. የምክትል ዋና ዳይሬክተር ሥልጣንና ተግባራት

ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ የባለሥልጣኑን ተግባሮች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት፣ በማስተባበር እና በመገምገም ዋና ዳይሬክተሩን ይረዳል፤

፪/ በባለሥልጣኑ መዋቅር መሠረት የሥራ ክፍፍል በማድረግ ከባለሥልጣኑ ዘርፎች ከፊሉን ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ተክቶት ይሠራል፤ ከአንድ በላይ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ካሉና ዋና ዳይሬክተሩ በተለይ ካልወከለ በምደባ ቅድሚያ ያለው ምክትል ዋና ዳይሬክተር ተክቶት ይሠራል፤

፬/ ከዋና ዳይሬክተር ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

## ፲፫. በጀት

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግስት ይመደባል፡፡

## ፲፬. የሂሳብ መዛግብት

፩/ ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፤

፪/ ባለሥልጣኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

## 12. Power and Duties of the Deputy Director General

The deputy Director General shall have the following power and duties:

1/ Support the Director General on planning, organizing, managing facilitating and evaluating activities of the Authority;

2/ Coordinate; monitor part of the Authority's unit based on the structure of the Authority;

3/ In the absence of the Director General and upon delegation shall act in place of the Director General; failing such delegation a Deputy Director General with the longest tenure shall be designated;

4/ Undertake other specifically assigned activities by the Director General.

## 13. Budget

The budget for the Authority shall be allocated by the Government.

## 14. Books and Accounts

1/ The Authority shall keep complete and accurate books and accounts;

2/ Each year, the books and accounts of the Authority shall be evaluated by the Auditor General or by Auditors assigned by the Auditor General.

፲፭. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

፲፮. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

15. Repealed and Inapplicable Laws

No Regulation, Directive, or practice shall, in so far as they are inconsistent with the provisions of this Regulation, have effect with respect to matters provided for by this Regulation.

16. Effective Date of the Regulation

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 31st Day of May, 2022.**

**ABIY AHMED (DR.)**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት